## “ የአለም የሴቶች ቀን ታሪካዊ ዳራ ”

በዓሉ በ19ኛው ክ/ዘመን መጀመሪያዎቹ በርካታ ቁጥር ያላቸው ሴቶች ይደርስባቸው የነበረውን የመብት ረገጣና ጭቆና በመቃወም የነጻነትና እኩልነት ጥያቄን አንግበው አደባባይ በመውጣት ለአመታት ባካሄዱት የትግል እንቅስቃሴ የተገኘ የድል ቀን ነው፡፡

ይህ የአመፅ እንቅስቃሴን መነሻ በማድረግ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዘንድ እውቅናን ለማግኘት የበቃ በዓል መሆኑ ይታወቃል፡ የበዓሉ መነሻ በፈረንጆቹ 1908 በኒውዮርክ ከተማ ነዋሪ የሆኑ 15,000 ሴቶች የተሻሻለ የሥራ ሰዓትና የደመወዝ ክፍያን እንዲሁም የመምረጥ መብታቸው እንዲከበር አደባባይ መውጣታቸውን ተከትሎ ነበር፡፡ከአንድ ዓመት በኋላ የአሜሪካ ማኅበራዊ ፓርቲ ዕለቱን የሴቶች ብሔራዊ ቀን ተብሎ ሊታወጅ የቻለው፡፡

በዓሉ ዓለማቀፋዊ ቅርፅን እንዲይዝ በ1910 ላይክላራ ዚክተን በተባለች ሴት አማካኝነት በዴንማርክ ዋና ከተማ ኮፐንሀገን በተካሔደው ዓለማቀፋዊ የሠራተኛ ሴቶች ኮንፍረስ ላይ ሀሳቡ የቀረበ ሲሆን ከአስራ ሰባት ሀገራት የተውጣጡ መቶ ተሳታፊ ሴቶች ሀሳቡን በደስታ ስለተቀበሉትም እንደ ኦስትርያ ዴንማርክ ጀርመንና ስዊዘርላንድ የመሰሰሉ ሀገራት በዓሉን በ1911 በማክበር ፈር ቀዳጅ ለመሆን ችለዋል፡፡

ዓለም የሴቶች ቀን በየዓመቱ በጎርጎሪዮሳዊው መጋቢት 8 ቀን የዓለም የሴቶች ቀን ይከበራል፡፡ ከዚህ የሴቶች ቀን ጋር በተያያዘ የመብት እና የእኩልነት ጥያቄዎች አብረው ይነሳሉ፡፡ አንድ የዓለም ባንክ ጥናት እንደሚያመለክተው በዓለም ላይ 143 ሃገራት የሴቶች እና ወንዶች እኩልነትን በሕገ መንግሥታቸው ላይ ያሰፈሩ ቢሆንም ስምንት ሃገራት ማለትም ቤልጂም፣ ካናዳ፣ ዴንማርክ፣ ሲውዲን፣ አይስላንድ፣ ሉክስንበርግ፤ ፈረንሳይ እና ሊትዌኒያ ብቻ ናቸው የሴቶች እና የወንዶች እኩልነት መብትን የሚያረጋግጡት፡፡ ጥናቱ ትኩረቱን ያደረገውም ሥራን፣ የቤተሰብ፣ የንብረት ባለቤትነት፣ የጡረታን እና የመሰሰሉ ጥያቄዎች ላይ ተመርኩዞ ነው፡፡ የሚያሳዝነው ነገር ግን እስካሁን በየትኛውም ሀገር የወንድ እና የሴቶች እኩልነት ሙሉ በሙሉ አለመረጋገጡን ነው የግሎባል ጀንደር ጋፕ መዘርዝር የሚጠቁመው፡፡

በዚህ ዓመት የሴቶች ቀን በዓለም ዐቀፍ ደረጃ 111ኛ ጊዜ “ **የፆታ እኩልነት ለዘላቂ ልማት**” በሚል መሪ ቃል የሚከበር ሲሆን በአገር አቀፍ ደረጃ ደግሞ ለ46ኛ ጊዜ “ **እኔም የእህቴ ጠባቂ ነኝ** ” በሚል መሪ ቃል ይከበራል፡፡ በዚህ መሪ ቃል ማክበር ያስፈለገበት ዋና ዓላማ የሴቶች ሁለንተናዊ መብት መከበር ሁሉም አካል ሓላፊነት እንዳለው ለማስገንዘብ ነው፡፡

## የሴቶችን ቀን ሲከበር ዋና ዓላማው

ሴቶች ሁለንተናዊ መብት መከበር በተለይ እንደ ሀገር በ10 ዓመቱ መሪ የልማት እቅዶችና በየዘርፉ የተያዙ ውጥኖች በሚፈለገው ደረጃና ፍጥነት እንዲሳኩ በማስቻል ረገድ የሴቶች ድርሻ የላቀ መሆኑን አጽንኦት ለመስጠት፣ ህብረተሰቡን ለማስገንዘብና ተገቢው ምላሽ እንዲሰጥ ለማስቻል እንዲሁም ሴቶች ድህነትን በማስወገድም ሆነ ልማት በማፋጠንና ስኬታማ በማድረግ ረገድ ያላቸውን የላቀ ሚና በውል በመገንዘብ በሁሉም መስኮች ያላቸው ተሳትፎ በእኩል ደረጃ እንዲጐለብትና ብቃታቸው እንዲያድግ ለማስቻል ነው፡፡

## የሴቶች ቀን መከበሩ አስፈላጊነት

በአገራችን ሴቶች የማኅበረሰቡን ከግማሽ በላይ የሚሸፍኑ ቢሆንም በማሕበረሰቡ ዘንድ ባለው የተሳሳተ የአመለካከት፣ ኋላ ቀር የሆኑ ልማዶችና ባሕሎች ምክንያት አገራዊና ማሕበረሰባዊ ተሳትፏቸው ዝቅተኛ ነው፡፡ሴቶች ከወንዶች የበለጠ ትልቅ የቤተሰብ ኃላፊነትን የተሸከሙ ከመሆኑም ባሻገር በህጻናትና በአረጋዊያን ላይ የሚደርሱ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊይና ፖለቲካዊ ጥቃቶችና ችግሮች ሁሉ እነሱን ነክተው የሚያልፉ በመሆኑ ከእነዚህና መሰል ችግሮች ተላቀው በሁሉም ዘርፍ ያላቸው ተሳትፎች ከፍ እንዲል እንዲሁም በተሰማሩበት ሥራ ውጤታማ እንዲሆኑ በተቻለ መጠን ማበረታት እና መደገፍ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡

## የአለም የሴቶች ቀን እና ፆታዊ ጥቃት

የሴቶች ቀን ተለይቶ ለምን ይታሰባል የሚሉ አንዳንድ ወገኖች ቢኖሩም በተቃራኒው አንድ ቀን ያንሳል 365ቱም ቀን የሴቶች ጉዳይ ይውሰ የሚሉ ጥቂት አይደሉም፡፡ ስለሴቶች መብት መከበር ብዙ በሚነገርበት በዚህ ዘመን ግን በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች ከዕለት ወደዕለት እየጨመሩ መሄዳቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ከጎርጎሪዮሳዊው 1910 ጀርመናዊቷ የሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ አባል ክላራ ሴትኪን

አሜሪካውያን ሴቶች የጀመሩት የሴቶችን ቀን የማክበር ሃሳብ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት እንዲያገኝ ጥያቄ አቀረቡ። 100 የሚሆኑ ከ17 ሃገራት የተውጣጡ ሴቶች በሃሳባቸው ተስማምተው በቀጣዩ ዓመት 1911 ማለት ነው ለመጀመሪያ ጊዜ የዓለም የሴቶች ቀን በኦስትሪያ፤ ዴንማርክ፣ ጀርመን እና ስዊትዘርላንድ በዚሁ የዘመን ቀመር መጋቢት 19 ቀን ተከበረ። የሴቶችን ቀን ማክበሩ አንድ ነገር ሆኖ ዛሬም በሀገሪቱ በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ፆታዊ ጥቃቶች መበራከታቸው አነጋጋሪ ሆኗል።በጥቂት ሴቶች አሳሳቢነት ተጠንስሶ ለመጀመሪያ ሁለት ዓመታት በጎርጎሪዮሳዊው የዘመን ቀመር መጋቢት 19 ቀን ይከበር የነበረው የዓለም የሴቶች ቀን ከ1913ዓ,ም ጀምሮ በመጋቢት 8 ላይ ሲከበር ቆይቷል። ዕለቱ በተመድ ዕውቅና ያገኘው ግንበ1975 ነው በዚሁ አቆጣጠር። ከዚያን ጊዜ ወዲህ ታዲያ በየዓመቱ መሪ ቃል እየተሰጠው ዓመታት አሳልፏል። ዕለቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሲታሰብ ለፆታ እኩልነት የሚቀርበው ጥሪ እና ቅስቀሳ እንዳለ ሆኖ ከፖለቲካው እስከማኅበራዊ ዘርፍ ሴቶች ያገኙትን ስኬት የሚያወሳ እንዲሆን የታለመ ነው። ስለሴቶች መብት ኢትዮጵያ ውስጥ በአደባባይ መሞገት ከተጀመረ ወዲህ ጥቂት የማይባሉ ሴቶች ላይ የተጫኑ ቀንበሮች በይፋ ኅብረተሰቡ እንዲነጋገርባቸው ማድረግ ቢቻልም መሠረታዊ የሆኑ ለውጦች ተደርገዋል ለማለት አያስደፍርም። ዛሬም በባሕል ስም የሚፈፀሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አልቀሩም። በምሳሌነትም የሴት ልጅ ግርዛት እና ጠለፋን መጥቀስ ይቻላል። ኢትዮጵያ ውስጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚከበረው የሴቶች ቀን መታሰብ ከተጀመረ 44 ዓመታት እንደዋዘ አልፈዋል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ምንም እንኳን ጠንካራ ሴቶች የተለያዩ መሰናክሎችን አልፈው ለስኬት ቢበቁም በተለይ በጓዳ የሚፈፀመው ፆታዊ ጥቃት ተባብሶ መቀጠሉ ይነገራል። ሴታዊት የተሰኘ መንግሥታዊ ያልሆነ ለሴቶች መብት መከበር የሚሟገት ድርጅት መሥራች እና አስተባባሪ የሆኑትን ዶክተር ስህን ተፈራ ና ሌሎች ሙህራን አስተያየታቸውን ሲገልፁ በአሁኑ ጊዜ ያለው የሴቶች የመብት ይዞታ ኢትዮጵያ ውስጥ ህዝብ በመንግስት ላይ ያለውን እምነት ይሸረሽራል፣ ምክንያቱም **የጥቃቱ መበራከት አጥፊዎች ተገቢውን ቅጣት እና እርምት እንዳያገኙ ማመቻቸት ያልቻለው ደካማ የፍትህ ሥርዓት ዋና ተጠያቂ መሆኑንም ያወሳሉ:: የተለያዩ ዓለም አቀፍ ዘገባዎችም ፆታዊ ጥቃት እያደረሱ ያለቅጣት የሚታለፉ በመበርከታቸው አዘውትሮ እናአብዝቶ ስለሴቶች መብት እና ፆታዊ እኩልነት ግንዛቤ ሊያስጨብጡ የሚያግዙ እንቅስቃሴዎችን ማድረግ እንደሚበጅ ይመክራሉ:: ኢትዮጵያ ውስጥ ስለሴቶች መብት በመቆርቆር የሚፈፀሙ ጥቃቶች አደባባይ እንዲወጡ ማድረግ የቻሉ ጥቂት የማይባሉ ድርጅቶች ማሕበራት** መኖረቸው ይታወቃል።

## **በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ እውነታዎች**?

****************

.ከ3 ሴቶች አንዷ በህይወት ዘመኗ ተደፍራለች (UN)

• በአለማችን ዕድሜቸው ከ15 እስከ 44 የሆኑ ሴቶች ከካንሰር፣ ከጦርነት፣ ከመኪና አደጋና የወባ በሽታ ይልቅ አስገድዶ የመደፈር ስጋት ያሳስባቸዋል (UN)

• 603 ሚሊዮን ሴቶች ጾታዊ ጥቃት ወንጀል ባልሆነባቸው አገራት ውስጥ ይኖራሉ (UN)

• በአሁኑ ወቅት በአለማችን 700 ሚሊዮን ያህል ሴቶች ዕድሜያቸው 18 ዓመት በታች ሆነው ያገቡ ሲሆን 250 ሚሊዮን ሴቶች ደግሞ ዕድሜያቸው 15 ዓመት በታች ሆነው ያገቡ ናቸው (UNICEF)

• በየአመቱ በአለም ላይ ከ600-800 ሺህ ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውሮች ይካሄዳሉ:: ከሚካሄደው የህገ ወጥ ሰዎች ዝውውር ከአምስት አራቱ ሴቶች ነው:: Trafficking.org)

(• በየአመቱ 62 ሚሊዮን ሴቶች የትምህርት ዕድል አያገኙም (Makers)

• የአለማችን116 ሚሊዮን ሴት ተማሪዎች (25 በመቶ ያህሉን የሴት ተማሪዎችን ቁጥር ይዛል) አንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አያጠናቅቁም::

• በአለማች ለሴቶች የሚከፈለው ክፍያ ከወንዶች አንጻር ከ60-75 በመቶ ያነሰ ነው (PBS)

• 155 አገራት ሴቶችን ኢኮኖሚ ተጠቃሚነት የሚገድብ ህጎች ሲኖራቸው 100 አገራት ደግሞ ሴቶች የሚሰሩትን የስራ አይነት ገድበዋል (The Guardian)

• በየደቂቃው አንድ እናት በወሊድ ምክንያት ትሞታለች (UN)

• በአለማች 200 ሚሊዮን ሴቶች በግዳጅ ይገረዛሉ (World Health Organization)




ኢትዮጲያ ግብርና ባለስልጣን በህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ስራ አስፈጻሚ የተዘጋጀ የተዘጋጀ

ጥር 2017